# አይረባ ሙግቱን

አያት ቅድመ አያቱ ፤ በአዲሳባ ኖሮ
እሱም ተወልዶባት ፤ እትብቱ ተቀብሮ
ልጅ ባሳደገባት ፤ በወግ ተሞሽሮ
ከየት ይምጣ ከየት ፤ ሁሉ ተከባብሮ
ይኖር እንዳልነበር ፤ ጉድ ሰማን ዘንድሮ ፤
ትላንትና ሸገር ፤ የገባ ተሻግሮ
በንቶ ፈንቶ ተረት ፤ ክፉኛ ተሳክሮ
ቀን አነሳኝ ብሎ ፤ ልቡ ተወጥሮ
ነገን የማያስብ ፤ ፊደል አንኳን ቆጥሮ
ነባሩን ይጋፋል ፤ አጓጉል ተፈጥሮ ፤
እሱም ላይኖርባት ፤ ካልሆነ ተቀብሮ
እንደሰው ቢታሰብ ፤ ባይኮን ደንቆሮ
ለማንም አይበጅም ፤ የንፋጅ ከበሮ ።

ስለ ሰላም ብሎ ፤ ቢደፋም አንገቱን
ለእምነቱ መሞት ፤ ላገር መሰዋቱን
እንኳንስ የቅርቡ ፤ የሩቁም ያውቀዋል
ጀግና ማንነቱን ፤
አሳምሮም ያውቃል ፤ ግዳጅና መብቱን
ነገን በሩቅ ያያል ፤ አይደለም የለቱን
መተንኮሱ አይበጅም ፤ አይቶ መጨመቱን ።

ዛሬም እንደቀድሞው ፤ በልቡ ሸፍቶ
አንድነትን መስበክ ፤ ጥላቻን አንግቶ
ጊዜ መግዣ እንዲሆን ፤ ጥርስን አሳይቶ
ሲዶልቱ ማደር ፤ አንዱን አስተኝቶ
ሌላም እናውቃለን ፤ እንኳን እቺን ቀርቶ
እዚያ ቤት ያለ እሳት ፤ እዚህስ መቼ ጠፍቶ
ሰላም መውደድ እንጂ ፤ አይደለም ተፈርቶ
ለማንም አይበጅም ፤ ድንፋታም ቀረርቶ ።

የትም ይኑር የትም ፤ እንደዜጋ መብቱን
የሚያስከብርብርት ፤ ህግና ስርአቱን
እንዳሻው ተዛውሮ ፤ ነፋፍቶ ደረቱን
የሚገነባበት ፤ ንብረትና ሃብቱን
ለሱ እንዳይታገል ፤ በከንቱ ጉልበቱን
ሲያባክን ይውላል ፤ ጊዜና ሰዓቱን ፤
ቢጠራጠር እንጂ ፤ ኢትዮጵያዊነቱን
ባላነሳም ነበር ፤ የኔ ፤ ያንተ ብሎ ፤
አይረባ ሙግቱን ።

ታዛቢው

February 8, 2019